እስመ፡ እግዚአብሔር፡ ነበበ፤

እግዚአብሔር ይጥፉ፡ ብሎ፡ አዝዟልና፤

፲፱፤ ወይወርስዎ፡ ሰብአ፡ ናጌብ፡ ለደብረ፡ ኤሳው፤

ሰብአ፡ ሣህል፡ ሰብአ፡ በዳ፡ ሲል፡ ነው፤ በምድረ፡ በዳ፡ ይኖሩ፡ የነበሩ፡ እስራኤል፡ የኤሳውን፡ አገር፡ ይወርሳሉ፤

ወሳፌላ፡ ዘኢሎፍሊ፤

የኢሎፍሊ፡ ክፍል፡ የምትሆን፡ ሳፌላን፡ ይወርሳሉ፤

ወይወርስዎ፡ ለደብረ፡ ኤፍሬም፡ ወለ አሕቃላተ፡ ሰማርያ፤

በኢያሱ፡ ጊዜ፡ የኤፍሬምን፡ ዕፃ፡ የሰማርያን፡ አውራጃ፡ ይወርሳሉ፤

ወብንያም፡ ወገለዓድ፤

የብንያምን፡ የገለዓድን፡ ዕፃ፡ ይወርሳሉ፤

ወበሐውርቲሆሙ፤

አገራቸውን፡ ሁሉ፡ ይወርሳሉ፤

፳፤ ወዛቲ፡ ቀዳሚቶሙ፡ ለደቂቀ፡ እስራኤል፡ በምድረ፡ ከነአን፤

የእስራኤል፡ ልጆች፡ መጀመሪያ፡ በከነዓን፡ ያደረጓት፡ ስልፋቸው፡ ይች፡ ናት፤ አንድም፡ መጀመ ሪያ፡ የተደረገችላቸው፡ ተአም ራት፡ ይች፡ ናት፤

ከመ፡ ሰራፕታ፡ በሐውርተ፡ እስራ ኤል፡ እስከ፡ ኤፍራታ፤

ሰራፕታ፡ የእስራኤል፡ አገር፡ እንደመሆኗ፡ እስከ፡ ኤፍራታ፡ ድረስ፡ ይወርሳሉ፤ አንድም፡ እምሰራጵታ፡ እስከ፡ ኤፍራታ፡ ሲል ነው፤ ከሰራጵታ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ኤፍራታ፡ ድረስ፡ ይወርሳሉ፤

ወይወርሱ፡ አህጉረ፡ ናጌብ፤

አህጉረ፡ ሣህል፡ ሲል፡ ነው፤ ይቅርታ፡ የሚደረግበትን፡ አገር፡ ይወርሳሉ፤

፳፩፤ ወእለ፡ ድኅኑ፡ የዓርጉ፡ እም ደብረ፡ ጽዮን፡ ከመ፡ ይትበቀልዎ፡ ለደ ብረ፡ ኤሳው፤

ከባቢሎን፡ የዳኑ፡ እስራኤል፡ የኤሳውን፡ አገር፡ ያጠፉ፡ ዘንድ፡ ከደብረ፡ ጽዮን፡ ይወጣሉ፤

ወይከውን፡ መንግሥት፡ ለእግዚ አብሔር፤

የእግዚአብሔር፡ መንግሥቱ፡ በሚጠት፡ ይገለጣል፤ ትርጓ ሜው፡ እንዳለፈው ነው፡

ተፈጸመ፡ ዘአብድዩ፡ ነቢይ፤

አብድዩ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ደረሰ፡ ተፈጸመ፤

በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ ምስሌነ፡ ወስ ብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡

አነቃቅቶ፡ ለአስጀመረን፤ አተ ጋግቶ፡ ላስፈጸመን፡ ለእግዚ አብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፤ አሜን፡ በውነት፡፡

የግል ቤተ መጻሕፍት

# ዘዮናስ ነቢይ

## መቅድም፤

ዮናስ፡ ማለት፡ ርግብ፡ ማለት፡ ነው፤ ጌታ፡ ተነሥተህ፡ ወደ ነነዌ፡ ሂድ፡ አለው፤

ወስብከ፡ ሎሙ፤

ነነዌ፡ እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ በእሳት፡ ትጠፋለች፡ ብለህ፡ አስተምራቸው፤ ክፋታ ቸው፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ ደርሷልና፤ ዮናስም፡ አንተ፡ መሐሪ፡ ወመ ስተሣህል፡ ነህ፤ እሳት፡ መው ረዱ፡ የቀረ፡ እንደሆነ፡ ነቢየ፡ ሐሰት፡ እባል፡ የለም? ብሎ፡ ዝም አለ፤ ሂድ፡ ብልህ፡ ብሎ፡ ጌታ፡ ገሠጸው፤ ዮናስ፡ ማለት፡ የዋህ፡ ማለት፡ ነውና፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ከፊቱ፡ ቢያገኘኝ፡ አይደለም? ብሎ፤ ወተኃጥዐ፡ እምገጸ፡ እግዚአብሔር፡ እን ዲል፤ ከእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የሸሸሁ፡ መስሎት፡ ሄደ፤

ወረከበ፡ ሐመረ፡ ዘይነግድ፤

ወደ፡ ኢዮጴ፡ የሚሄድ፡ መር ከብ፡ አገኘ፤ መርከቡን፡ ተወጃ ጅቶ፡ ወጥቶ ተቀመጠ፤ እግዚ አብሔርም፡ ጽኑ፡ ነፋስ፡ አስ ነሣ፡ ማዕበሉም፡ ሞገዱም ተነሣ፤ መርከቡም፡ ይሰበር፡ ዘንድ፡ ስርግርግ፡ አለ፤ መር ከቡ፡ የቀለለልን መስሏቸው፡ ገንዘባቸውን፡ ከባሕር፡ ላይ፡ ይጥሉ፡ ጀመር፡ ያን፡ ጊዜ፡ ዮናስ፡ በከርሠ፡ ሐመሩ፡ ውስጥ፡ ተኝቶ፡ ያንኮራፋ፡ ነበር፤ ቀዛ ፊው፡ ወርዶ፡ ዮናስን፡ ታድ ነን፡ ዘንድ፡ ተነሥ፡ የፈጣሪ ህን፡ ስም ጥራ፡ አለው፤ ይህ፡ የመጣባችሁ፡ መከራ፡ በኔ፡ ምክንያት፡ ነውና፡ እኔን፡ አን ሥታችሁ፡ ጣሉኝ፡ አላቸው፤

ምንት፡ ተግባርከ፤

ማንን፡ ታመልካለህ? አገር ህስ፡ ወዴት፡ ነው? ወገኖች ህስ፡ እነማናቸው፡ አሉት፤ በወገኔም፡ ዕብራዊ፡ ነኝ፤ አይቴ፡ ብሔርከ፡ ላሉት፡ አይመል ስም፡ የማመልከውም፡ ሰማ ይን፤ ምድርን፤ ባሕሩን፤ የብ ሱን፡ የፈጠረ፡ ነው፡ አላቸው፤ ይህን፡ ቢላቸው፡ እጅግ፡ ፈሩ፡ አንስተን፡ የጣልነው፡ እንደሆ ነማ፡ ዕዳ፡ ይሆንብን፡ የለም? ብለው፡ እጣ፡ ተጣጣሉ፤ ወወ ረደ፡ ዕፃ፡ ላዕለ፡ ዮናስ፡ እን ዲል፤ በዮናስ፡ ዕጣ፡ ወጣበት፡

www.ethiopianorthodox.org